ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/ዳ/1469/18

ቀን 22/12/2018 ዓ/ም

ለአብክመ ገንዘብ ቢሮ

ባህር ዳር

ጉዳዩ፦ <u>የተመዘገበ መመሪያ ማሳወቅን ይመለከታል</u>

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ/ም አንቀጽ 16(4) (በአዋጅ ቁጥር 313/2018 ዓ.ም እንደተሻሻለ) የአስተዳደር ተቋማት የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ/ም ከመውጣቱ በፊት በስራ ላይ የነበሩ መመሪያዎቻቸውን አዋጁ በወጣ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ለክልሉ ፍትሕ ቢሮ በመላክ ማስመዝገብ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሰረት የአማራ ክልል ገንዘብ ቢሮ በቁጥር አብክመ/ገቢ/20 በቀን 04/12/2018 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ <u>የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2011 ዓ/ም</u> በክልሉ ፍትሕ ቢሮ እንዲመዘገብለት ጠይቋል፡፡

ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2011 ዓ/ም የወጣው በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 ዓ/ም አንቀፅ 62 (1) (ሀ) የክልሉ ገንዘብ ቢሮ ተለይተው በተዘረዘሩ ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች ላይ በመመሪያ ገደብ እንዲያስቀምጥ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታ የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 301/2018 ዓ/ም አንቀጽ 65 (ሀ) (2)፣ (3)፣ (4) እና (6) በተዘረዘሩ ከገቢ ግብር ነፃ በሆኑ ገቢዎች ላይ የክልሉ ገንዘብ ቢሮ ገደብ እንዲያስቀምጥ ፈቅዶለታል፡፡ ከገቢ ግብር ነፃ በተደረጉ ገቢዎች ዝርዝር እና አይነት እንዲሁም ለክልሉ ገንዘብ ቢሮ በመመሪያ ገደብ የማስቀመጥ ስልጣንን በተመለከተ በተሻረው አዋጅ እና በአዲሱ አዋጅ ድንጋጌዎች መካከል ምንም አይነት የአቀራረፅና የይዘት ልዩነት የለም፡፡

አዲሱ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 301/2018 ዓ/ም አንቀጽ 101 (2) በተሻረው አዋጅ ቁጥር 240/2008 ዓ/ም መሰረት የወጡና ከአዲሱ አዋጅ ጋር የማይቃረኑ መመሪያዎች በአዲሱ መመሪያ እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው የሚቀጥል መሆኑን ደንግጓል፡፡

በክልሉ ገንዘብ ቢሮ ለምዝገባ የተላከው መመሪያ ቁጥር 1/2011 ዓ/ም በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ የሚወድቅና የክልሉ ገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ እስከሚተካ ድረስ ተፈፃሚነቱ የሚቀጥል መመሪያ ነው።

በመሆኑም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ/ም እና በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ማሻሻያ አዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 160/2018 ዓ.ም አድርጎ የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 10 ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን ሲሆን መመሪያውን በክልሉ ገንዘብ ቢሮ ድረ ገፅ እንድትጭኑ በአክብሮት አሳውቃለሁ።

ከሰላምታ ጋር

ይስማው ዘመነ

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

የክልል ዐቃቤ ሕግ

<u>ግልባጭ</u>

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክት/ል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

<u>ፍትህ ቢሮ</u>

መመሪያ ቁጥር 160/2018 ዓ/ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም መመሪያ

1. አውጪው ባለስልጣን

የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 አንቀጽ 62/1/ሀ እና አንቀጽ 93/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር160/2018 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. ትርጓሜ

በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ወይም በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በታክስ አስተዳደር አዋጁ ወይም በገቢ ግብር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

1) "ደመወዝ" ማለት በአንድ የስራ ደረጃ ላይ የተመደቡ ሠራተኞች ለሚሰጡት አገልግሎት በቀጣሪው የሚከፈል ክፍያ ሲሆን አበል እና ጥቅማ ጥቅሞችን አይጨምርም፡፡
2) "የትራንስፖርት አበል" ማለት በቀጣሪውና በተቀጣሪው መካከል በተደረገ ውል ውስጥ በግልጽ የተመለከተ እና ተቀጣሪው ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ሥራ ቦታ እንዲሁም ከስራ ቦታው ወደ መኖሪያ ቤቱ ለመጓጓዝ እንዲሁም ተቀጣሪው

ሥራውን ለማከናወን መደበኛ ስራ ቦታው በሚገኝበት ከተማ ውስጥ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመዘዋወር የሚያስፈልገው የትራንስፖርት ወጪ ለመሸፈን በቀጣሪው የሚከፈል አበል ነው።

3) **"የውሎ አበል"** ማለት አንድ ተቀጣሪ ወይም ተሿሚ ወይም የህዝብ ተመራጭ የተቀጠረበትን ወይም የተመደበበትን ሥራ ለማከናወን መደበኛ የሥራ ቦታው ከሚገኝበት ከተማ ውጪ በሚሄድበት ጊዜ ለምኝታ፣ለምግብ፣ለመጠጥና ለተዛማጅ ወጪዎች የሚከፈል አበል ነው።

4) **"በሥራ ሁኔታ አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል"** ማለት የሥራ ሁኔታው ለጨረር፣ ለበሽታ፣ ለኬሚካል ልቀት ወይም ብክለት፣ ለንጹህ አየር እጥረት ፣ለከፍተኛ ሙቀት ፣ለከፍተኛ ቅዝቃዜ የሚያጋልጥ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተቀጣሪው ጤናና ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከፈል አበል ነው።

5) **"በሥራ ቦታው አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል"** ማለት የሥራ ቦታው የሚገኝበት ከተማ ወይም ወረዳ ከፍተኛ ሙቀት ያለው ወይም ለኑሮ አስቸጋሪ በመሆኑ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ምክንያት በተቀጣሪው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ መሰረት የሚከፈል አበል ነው።

6) "አዋጅ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 ነው።

7) "ደንብ" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅን ለማስፈጸም የወጣ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 162/2010 ነው።

8) **"ቢሮ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ነው።

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዋጁ እና በደንቡ ከገቢ ግብር ነፃ በተደረጉ ገቢዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>አበል እና ሽልማት ከግብር ነፃ የተደረገበት ሁኔታ</u>

5. <u>የትራንስፖርት አበል እና የማጓጓዣ ወጪ</u>

1) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እስከ 8 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የትራንስፖርት አበል ከግብር ነጻ እንዲሆን የሚፈቀደው በቀጣሪው እና በተቀጣሪው መካከል በተደረገ የስራ ውል ውስጥ በግልጽ በተመለከተ እና ከመኖሪያ ቤት ወደ ስራው ቦታ እንዲሁም ከስራው ቦታ ወደ መኖሪያ ቤት ለመሄድ የሚከፈል አበል እና በስራ ባህሪው ምክንያት በመዘዋወር ለሚሰራ ተቀጣሪ የሚከፈል አበል ነው።

2) በስራ ባህሪው ምክንያት ሥራውን ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወር የሚያከናውን ተቀጣሪ ለአንድ ወር ጉዞ የሚከፈለው የትራንስፖርት አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ከጠቅላላ የወር ደመወዙ ከአንድ አራተኛ (1/4) ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው። ይሁንና የተቀጣሪው ጠቅላላ የወር ደመወዝ አንድ አራተኛ ከብር 2200 የሚበልጥ ሲሆን ከግብር ነፃ የሚደረገው የትራንስፖርት አበል በማንኛውም ሁኔታ ከብር 2200 ሊበልጥ አይችልም።

3) አንድ ተቀጣሪ በስራ ባህሪው ምክንያት በመዘዋወር ለሚሰራው ስራ ለነዳጅ ወጪ የሚከፈለው ጥሬ ገንዘብ ለትራንስፖርት እንደተከፈለ አበል ተቆጥሮ ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረገው ከጠቅላላ የወር ደመወዙ ከአንድ አራተኛ (1/4) ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው። ይሁንና የተቀጣሪው ጠቅላላ የወር ደመወዝ አንድ አራተኛ ከብር 2200 የሚበልጥ ሲሆን ከግብር ነፃ የሚደረገው የነዳጅ ወጪ በማንኛውም ሁኔታ ከብር 2200 ሊበልጥ አይችልም።

4) አንድ ተቀጣሪ ከመኖሪያ ቤት ወደ ስራው ቦታ እንዲሁም ከስራው ቦታ ወደ መኖሪያ ቤት የሚጓጓዝበት የመሥሪያ ቤቱ የትራንስፖርት ሰርቪስ ቢቀርብም ባይቀርብም ለዚህ ዓይነት የትራንስፖርት አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ለአንድ ወር ከብር 600 ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው።

5) አንድ ተቀጣሪ ከመኖሪያ ቤት ወደ ስራው ቦታ እንዲሁም ከስራው ቦታ ወደ መኖሪያ ቤት ለመሄድ ለነዳጅ ወጪ በጥሬ ገንዘብ የሚከፈለው የትራንስፖርት አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ለአንድ ወር ከብር 600 ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው።

6) አንድ ተቀጣሪ ሥራውን ለማከናወን መደበኛ የሥራ ቦታው ከሚገኝበት ከተማ ውጪ ሲንቀሳቀስ ለመጓጓዣ ወጪ የሚሰጠው ክፍያ ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው በስራ ላይ ባለው የትራንስፖርት ታሪፍ ወይም በሚያቀርበው ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ከከፈለው የአየር፣ የውሃ እና የየብስ ትራንስፖርት የአገልግሎት ዋጋ ሊበልጥ አይችልም።

7) አንድ የውጭ አገር ዜጋ ሥራን ለማከናወን ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ የውል ዘመኑን ጨርሶ ከሀገር ሲወጣ የሚከፈለው የትራንስፖርት ወጪ ከግብር ነጻ ሊሆን የሚችለው በተፈጸመው የቅጥር ውል መሰረት እና የአየር፣ የውሃ እና የየብስ ትራንስፖርት አገልግሎት ዋጋ ታሪፍ መሰረት ሆኖ ከግብር ነጻ የሚሆነው ለግል መገልገያ ዕቃዎች የሚከፈለው የጭነት ሂሳብ ከ300 ኪሎግራም ሊበልጥ አይችልም፡

8) አንድ ግብር ከፋይ ከመደበኛ መኖሪያ ቦታቸው ርቀው ሥራቸውን የሚከናውኑ ሠራተኞች ቤተሰባቸውን ለመጠየቅ የሚያደርጉትን ጉዞ ወጪ የሚሸፍን በሚሆንበት ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ወጪ ከግብር ነጻ ሊሆን የሚችለው በተፈጸመው የቅጥር ውል ውስጥ ቀጣሪው ይህ ግዴታ ያለበት ሆኖ ሲገኝ ነው።ሆኖም ለዚህ ዓይነቱ ጉዞ የሚከፈለው ወጪ ከግብር ነጻ የሚደረገው በአንድ የግብር ዓመት ከሁለት የደርሶ መልስ ጉዞ ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

6. <u>የውሎ አበል</u>

1) አንድ ተቀጣሪ የሚከፈለው የውሎ አበል ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረገው የተቀጠረበትን ስራ ለማከናወን ከመደበኛ የስራ ቦታው ውጪ 25 ኪሎ ሜትር እና ከዚያ በላይ ርቆ በመሄድ የሚከፈለው የቀን የውሎ አበል ሲሆን ብቻ ነው።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በሀገር ውስጥ ለሚደረጉ ጉዞዎች የሚከፈል የውሎ አበል፡-

ሀ. አንድ ተቀጣሪ የሚከፈለው የቀን የውሎ አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ከብር 500 ወይም ከደሞዙ 4% ከሁለቱ ከፍተኛ ከሆነው መጠን ባልበለጠ ብቻ ነው።

ለ. በዚህ ንኡስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሀ አፈጻጸም አንድ ተቀጣሪ የአልጋ አበል ያለገደብ ወይም በተወሰነ ገደብ በደረሰኝ የሚወራረድለት ከሆነ በደረሰኙ መሠረት ለአልጋ የተከፈለው ገንዘብ ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረግ ሲሆን ለቁርስ፣ ምሳ፣ እራት እና የመሳሰሉ ወጪዎች የሚሰጠው የውሎ አበል ከግብር ነጻ ሊደረግ የሚችለው ከብር 300 ወይም ከደሞዙ 2.5% ከሁለቱ ከፍተኛ ከሆነው መጠን ባልበለጠ ብቻ ነው።

ሐ. ለማናቸውም ድርጅት ስራ አስኪያጅ ወይም ምክትል ስራ አስኪያጅ የሚከፈለው የውሎ አበል ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረገው ከብር 1000 ወይም ከወርሓዊ ደሞዙ 5 በመቶ ከፍተኛ ከሆነው መጠን ባልበለጠ ብቻ ነው።

መ. በዚህ ንኡስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሐ አፈጻጸም አንድ ስራ አስኪያጅ ወይም ምክትል ስራ አስኪያጅ የአልጋ አበል ያለገደብ ወይም በተወሰነ ገደብ በደረሰኝ የሚወራረድለት ከሆነ በደረሰኙ መሠረት ለአልጋ የተከፈለው ገንዘብ ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረግ ሲሆን ለቁርስ፣ምሳ፣ እራት እና ለመሳሰሉ ወጪዎች የሚሰጠው የውሎ አበል ከገቢ ግብር ነጻ

የሚደረገው ከብር 600 ወይም ከወርሓዊ ደሞዙ 3 በመቶ ከፍተኛ ከሆነው መጠን ባልበለጠ ብቻ ነው፡፡

3) ወደ ውጪ ሀገር ለሚደረጉ ጉዞዎች የሚከፈል የውሎ አበል፡-

ሀ. አንድ ተቀጣሪ የተቀጠረበትን ስራ ለማከናወን ወደ ውጭ ሀገር ለሚያደርገው ጉዞ የሚከፈለው የውሎ አበል ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረገው መንግስት ከተሿሚዎች ውጪ ለሌሎች ተቀጣሪዎቹ ከወሰነው የውሎ አበል ልክ ባልበለጠ ብቻ ነው፡፡

ለ. የማናቸውም ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ወይም ምክትል ሥራ አስኪያጅ ከድርጅቱ ስራ ጋር በተገናኘ ወደ ውጭ ሀገር ለሚያደርገው ጉዞ የሚከፈለው የውሎ አበል ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረገው መንግስት ከተሿሚዎች ውጪ ለሌሎች ተቀጣሪዎቹ በወሰነው የውሎ አበል ልክ ላይ 20 በመቶ ተጨምሮት ይሆናል፡፡

4) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ቢኖርም በሀገር ውስጥ ለሚደረግ የስራ እንቅስቃሴ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ኦፕሬተሮች የሚከፈል የውሎ አበል ከ25 ኪ.ሜ ባነሰ ወይም በበለጠ ርቀት ቢሆንም የተከፈለው የውሎ አበል ከግብር ነጻ ይሆናል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 የተደነገገው ቢኖርም የመንግስት መስሪያ ቤት ለተሻሚዎች እና ለተቀጣሪዎቻቸው ከመደበኛ የስራ ቦታ ውጪ 25 ኪሎሜትር እና ከዚያ በላይ ርቀው በመሄድ ለሚያከናውኑት ስራ የሚከፍሉት የቀን ውሎ አበል ሙሉ በሙሉ ከግብር ነጻ ተደርጓል፡፡

6) ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 አፈጻጸም፡-

ሀ) የመንግስት መስሪያ ቤት የሚለው ሀረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

ለ) 25 ኪሎ ሜትር የሚለካው ከከተማው አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት ወሰን ጀምሮ ሲሆን ማዘጋጃ ቤት የሌለው ከሆነ እንደ የሁኔታው ከከተማ

አስተዳደር ወይም ከቀበሌ አስተዳደር ወሰን ጀምሮ ተቀጣሪው እስከሚንዝበት ቦታ ድረስ ያለው ርቀት ነው።

7. <u>በስራ ቦታው አስቸጋሪነት ምክንያት ለተቀጣሪ የሚከፈል አበል</u>

1) በስራ ቦታው አስቸጋሪነት ምክንያት ለተቀጣሪ የሚከፈል አበል ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ የዚህ ዓይነት አበል እንዲከፈላቸው ለተፈቀዱ አካባቢዎች ሲሆን መጠኑም የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽ ለአካባቢዎች እንዲከፈል ከፈቀደው የስራ ቦታ አስቸጋሪነት አበል መጠን ያልበለጠ ይሆናል።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው በሲቪል ሰርቪስ አዋጅ በማይተዳደር የመንግስት መስርያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት፣ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ የግል ድርጅት ተቀጣሪ ወይም ሌላ ማንኛውም ተቀጣሪ ወይም ተሿሚ በሥራ ቦታው አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል ላይ በተመሳሳይነት ተፈጻሚ ይሆናል።

8. <u>በስራ ሁኔታው አስቸጋሪነት ምክንያት ለተቀጣሪ የሚከፈል አበል</u>

1) በስራ ሁኔታ አስቸጋሪነት ምክንያት ለተቀጣሪ የሚከፈል አበል ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው የሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት ለእነዚህ ሠራተኞች አበሉ ሊከፈል የሚገባ መሆኑን ሲወስን እና ይህም ማስረጃ ቀርቦ በገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚወክለው ሰው የውሳኔ ሀሳብ ቀርቦ በቢሮው ሲፈቀድ ብቻ ነው።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚቀርብ ማስረጃ የአስቸጋሪ ሁኔታውን መጠን፣ ጉዳት ሊያደርስ የሚችልበትን የአከባቢ ሽፋን እንደየርቀቱ የሚገልጽ፣ የስራ ሁኔታው ሊያደርስ የሚችለውን የጉዳት ደረጃ ከፍተኛ፣ መካከለኛ ወይም አነስተኛ ብሎ በመለየት በሚመለከተው አካል የተሰጠ ማስረጃ መሆን አለበት።

3) በስራ ሁኔታ አስቸጋሪነት ምክንያት ለተቀጣሪ የሚከፈል አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚሆነው የገንዘብ መጠን አነስተኛ ጉዳት ለሚያስከትል የስራ ሁኔታ ከወር

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ዳይሬክቶሬት

ደመወዙ ከ25%፣ መካከለኛ ጉዳት ለሚያስከትል የስራ ሁኔታ ከወር ደመወዙ ከ40%፣ ከፍተኛ ጉዳት ለሚያስከትል የስራ ሁኔታ ከሠራተኛው የወር ደሞዙ ከ60% ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው።

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም የጉዳትን ደረጃ የሚለይ ማስረጃ ያልቀረበ ከሆነ ወይም የጉዳት ደረጃውን መለካት የማይቻል ከሆነ ከተቀጣሪው የወር ደመወዝ ከ25% ባልበለጠ መጠን ከገቢ ግብር ነጻ ይደረጋል።

5) ሆኖም ከዚህ በላይ በተደነገገው አንቀጽ 5፣6፣7 እና 8 ሥር ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ቀጣሪ ለተቀጣሪ ክፍያ የሚፈጽም ከሆነ ልዩነቱ ከወርሃዊ ደመወዝ ላይ ተደምሮ የሥራ ግብር የሚከፈልበት ይሆናል።

9. <u>በማንኛውም መስክ ለላቀ የስራ ክንውን የሚሰጥ ሽልማት</u>

1) በአዋጁ አንቀጽ 62/1/ሸ ለላቀ የሥራ ክንውን የሚሰጥ ሽልማት ከገቢ ግብር ነፃ ሊደረግ የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች የተሰጠ ሽልማት ሲሆን ብቻ ነው።

ሀ. አንድን ቴክኖሎጂ በማሻሻል፣ አዲስ የፈጠራ ስራ በመስራት ወይም ወጪን ለመቀነስ የሚያስችል አሰራር ስራ ላይ በማዋል የሚሰጥ ሽልማት፣

ለ. በአለም አቀፍ ደረጃ በሚደረግ ውድድር አገርን ወክሎ ወይም በአገር አቀፍ ደረጃ በህግ በተቋቋመ የሽልማት ድርጅት በሚደረግ ማንኛውም ውድድር የሚሰጥ ሽልማት፣

ሐ. በፌደራል ወይም በክልሉ መንግስት የላቀ የስራ ክንውን ለፈፀመ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚሰጥ ማንኛውም ሽልማት ሲሆን ነው።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ/ የተመለከተው ሽልማት ከገቢ ግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው ከፈጠራ ሥራው ጋር ግንኙነት ያለው አግባብነት ባለው

የመንግስት አካል ለፈጠራ ሥራ እውቅና የተሰጠው ወይም የፈጠራ መብት ያገኘ ሲሆን ነው።

10. <u>ለተቀጣሪ በነፃ የሚቀርብ ምግብ እና መጠጥ</u>

1) በማዕድን ማውጣት፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርናና ሆርቲካልቸር እንዲሁም በሆቴሎች ፣ሬስቶራንቶች እና የምግብ አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማራ ቀጣሪ ለተቀጣሪዎቹ በነፃ የሚያቀርበው ምግብ እና መጠጥ ከገቢ ግብር ነፃ ሊደረግ የሚችለው ቀጣሪው ያለልዩነት ለሁሉም ተቀጣሪዎች ነፃ የምግብና መጠጥ አገልግሎት የሚያቀርብ መሆኑ የተረጋገጠበት ሰነድ ወይም የሠራተኛ ማህበር መሪዎች ከድርጅቱ ጋር የተስማሙበት ሰነድ ሲቀርብ ብቻ ነው።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ከግብር ነፃ የሚደረገው መጠጥ የአልኮል ይዘት ያለው ሊሆን አይችልም።

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

11. <u>በልዩነት ስለሚከፈል ግብር</u>

ቀጣሪው በዚህ መመሪያ ከተወሰነው ገንዘብ በላይ ለተቀጣሪው የሚከፍል ከሆነ በብልጫ በተከፈለው ገንዘብ ላይ ግብር ይከፈልበታል።

12. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

አዋጁ ስራ ላይ ከዋለ በኃላ በእንጥልጥል ያሉ እና ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሰረት ውሳኔ ያገኛሉ።

13. <u>የተሻረ መመሪያ</u>

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መመሪያዎች ተሽረው በዚህ መመሪያ ተተክተዋል።

1) ከገቢ ግብር ክፍያ ነጻ የሚደረጉ ክፍያዎችና ዓይነቶች መጠን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር ገመ-5/1995፣ ገባ-13/2006 እና ገባ -15/2007

2) በግብርና ልማት፣ ሆርቲካልቸር፣ በማዕድንና ነዳጅ ቁፋሮ እና በፋብሪካ ደረጃ በማምረት ተግባር ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ለሰራተኞቻቸው የሚያቀርቡት ነፃ የምግብ አገልግሎት ከገቢ ግብር ነፃ ለማድረግ የወጡ ሰርኩላር ደብዳቤዎች::

14. **<u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

1. ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ከፀደቀበት ከሃምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለፀው ቢኖርም ይህ መመሪያ በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ አዲስ ቁጥር ከተሰጠው በኃላ የሚቋቋም መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በክልሉ ገንዘብ ቢሮ ድረገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል::

ባህር ዳር

ሰኔ 11 ቀን 2011 ዓ.ም

ጥላሁን መሐሪ አንተነህ (ዶ/ር)

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ

ቢሮ ኃላፊ